የእመቤታችንን ታምር በሚናገር መጽሐፍ በመቅድሙ ቁጥር ፲፩ ላይ " ወአመ ፲ ወ ፮ ፍልሰተ ሥጋሃ እስከ ፳ ወ ፩ ሰዱሰን መዋዕለ ይግበሩ በዓለ ከመ ትንሣኤ ወልዳ " የሚል ጽሑፍ ይገኛል ። በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የፀናች ክብርት እመቤታችን በየጊዜው ስሟ ሲታሰብ እንዲኖር ክብሯ ሁሉ እንዲነገር የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አባቱ የአብና የባሕርይ ሕይወቱ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሆኗል ። ይኸም እንዲፈጸም አስቀድሞ መንፈስ ቅዱስ የቃኛቸው ነቢያት ተናግረውታል ። ከነቢያት መካከል ሀብተ ትንቢት የተሰጠው ክቡር ዳዊት " ወይዘክሩ ስመኪ በኲሉ ትውልደ ትውልድ " ብሎ ተናግሮላታል ። (መዝ. ፻፵፬÷፲፫) ትርጉሙ " ልልጅ ልጅ ሁሉ ስምሽን ይጠራሉ ያሳስባሉ" የሚል ነው ።

ቀደም ብሎ መንፈሳውያን አባቶቿ በሥጋ አባቷ የተባለ ነቢዩ ዳዊት ጭምር ዓበይት ነቢያት ደቂቀ ነቢያት ምሳሌ እየመሰሉ ትንቢት እየተናገሩ ክብሯን ሲናገሩላት ስሟን ሲያሳስቡ ኖረዋል ። ኋላም የተነሱ መንፈሳውያን ልጆቿ ሐዋርያት ሰብዓ አርድዕትና ሊቃውንት ምዕመናን ሁሉ ስሟን ሲያሳስቡ እንደሚኖሩ የተነገረ ትንቢት ነው ።

በዚህ የትንቢት ቃል መሠረት ታምሯን ክብሯን መታሰብ የሚገባቸውን በዓላቷን በጠቅላላ ለአምላክ እናት ተገቢውን ክብር በመስጠት ለስሟ መታሰቢያ የሚሆን አብያተ ክርስቲያናትን በማነፅ በስሟ ዝክር አድርጎ ለድሆች ለጦም አደሮች በመመጽወት ውዳሴዋን ቅዳሴዋን በማድረስ ትርጉማቸውን ከነንባባቸው በማስማትና በመስማት ወዘተርፈ ሲያስቧት ሲያሳስቡላት ይኖራሉ ።

በዚህ ምክንያት ለስሟ መታሰቢያ ከሚከበሩት ከ ፴፫ ቱ በዓላቷ መካከል ሥጋዋ ከዚህ ዓለም ወደ ገነት ኋላም በትንሣኤ በዕርገት ወደ መንግሥተ ሰማያት የፈለሰበትን ነሐሴ ፲፮ ቀን ይገኛል ። ይኸውም ፍልሰታ ለማርያም ተብሎ የሚታወቀው ነው ። በመቅድመ ተአምር ከላይ የተገለጠው ቃል ትርጉም በነሐሴ ባሥራ ስድስትም ሥጋዋ የፈለሰበት ነው ካሥራ ስድስት ጀምረው እስከ ሃያ አንድ ቀን ድረስ እንደ ልጅዋ ትንሣኤ በዓል አድርገው ያክብሩ የሚል ነው ከነሐሴ ፲፮ እስከ ነሐሴ ፳፩ ቀን ስድስቱን ዕለታት ቤተክርስቲያን የድንግልን ትንሣኤና ዕርገት ከልጇ ትንሣኤ ጋር በማነጻጸር ታከብርላታለች ። " ከመ ትንሣኤ ወልዳ " መባሉም ስለዚህ ነው ። " ከመ ትንሣኤ ወልዳ " ማለት " እንደ ልጇ ትንሣኤ " ማለት ነው ።

# አስደናቂው ትንሣኤ

እ መ ቤ ታ ች ን ቅድስት ድንግል ማርያም እሁድ ጥር ፳፩ ቀን አርፏለች። ሐዋርያት ባጎበር አድርገው ወደ ጌቴሴማኒ ይዘው ሲሄዱ አይሁድ ቀድሞ ልጅዋን ተነሣ ዐረገ እያሉ ሲያውኩን ይኖራሉ ዛሬ ደግሞ እሷም ተነሣች ዐረገች እያሉ ሊያውኩን አይደለምን ። በእሳት እናቃጥላት ብለው ተነሱ ታውፋንያ የሚባል አይሁዳዊ ተራምዶ አጎበሩን ጨበጠው ። መልአክ ሁለት እጁን በሰይፍ ቀጣው ከአጎበሩ ተንጠልጥሎ ቀረ ። ከዚህ በኋላ ዮሐንስን ጨምሮ በደመና ነጥቆ ከገነት አግብቶ ከዕፀ ሕይወት ሥር አኖራት ዮሐንስን እንደምን ሆነች አሉት በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አለች አላቸው ። ዮሐንስ አይቶ እኛ ሳናይ ብለው በነሐሴ መባቻ ጾም ጀመሩ ነሐሴ በጥር ብተት ሰኞ ይብታል ሰኞ እስከ ሰኞ ፫ ሰኞ እስከ ሰኞ ፲፮ ሱባዔው እሑድ ያልቃል እሑድ አምጥቶ ሰጥቷቸው ቀብረዋታል ማክሰኞ ተነሥታለች ቶማስ አልነበረም ደመና ጠቅሶ ከሀገረ ስብከቱ ሲመጣ ስታርግ አገኛት ።

ቀድሞ የልጅሽን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ ዛሬ ደግሞ ያንቺን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁን ብሎ ቢያዝን አይዞህ አትዘን እሊያ ትንሣኤዬን ዕርገቴን አላዩም አንተ አይተሃል ተነሣች ዐረገች ብለህ ንገራቸው ብላ የያዘችውን ሰበን ሰጥታ ሰደደችው ። ከዚህ በኋላ ሄዶ የእመቤታችን ነገር እንደምን ሆነ አላቸው ። አግኝተን ቀበርናት አሉት ። ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር ተው ይህ ነገር አይመስለኝም አላቸው ጴጥሮስ አንተ እንጂ ልማድህ ነው አንተ ብቻ ተጠራጥረህ አትቀርም አንተ እየተጠራጠርህ ሰውን ሁሉ ስታጠራጥር ትኖራለህ አለው እርሱም የያዘውን ያውቃልና ጸጥ ብሎ ይሰማቸዋል ። ከዚህ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስ ተቆጥቶ ሄዶ መቃብሩን ቢከፍተው አጣት ደንግጠ ቆመ አታምኑኝም ብዬ ነው እንጂ እመቤታችንስ ተነሣች ዐረገች አላቸው ። የያዘውንም ሰበን ሰጣቸው ለበረከት ተካፍለውታል ከዚህ በኋላ ባመቱ ቶማስ ትንሣኤሽን ዕርገትሽን አይቶ እኛ ሳናይ ብለው ጾም ጀመሩ በ፲፮ኛው ቀን እመቤታችንን መንበር አድርጎ ጴጥሮስን ካህን እስጢፋኖስን ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ በዚያው ላይ ቀድሶ አቁርቧቸዋል ። ትንሣኤዋንና ዕርገትዋን አሳይቶ ለዓለም ይህን እንዲያስተምሩ አዟቸዋል ።

ልጇ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤያችን በኩር ሆኖ በሞተ በሦስተኛው ቀን ተነስቷል ። እናቱ እመቤታችንም በልጇ ሥልጣን እንደ ልጇ ትንሣኤ ዘጉባኤን ሳትጠብቅ በክብር ተነሥታ አርጋለች ። ዜና ሕይወቷን በሚናገር ነገረ ማርያም ትንሣኤዋና ዕርገቷ በተቀበረች በሦስተኛው ቀን ነሐሴ ፲፮ ቀን እንደሆነ ተጽፎ ይገኛል ። ልጇ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ



www.ethiopianorthodox.org

በሦስተኛው ቀን እንደተነሣ እናቱ ድንግል ማርያምም በሦስተኛው ቀን እንደ ልጇ በመነሣቷ አከባበሩና አፈጻጸሙ ከልጇ ትንሣኤ ጋር ተነጻጻሪ ሆኗል ። ትንሣኤዋንና ዕርገቷን በማስመልከት በቅዱስ መጽሐፍ ዓይነተኛ ምስክር ይገኛል ። በታሪክ የተረጋገጠው በመጽሐፍ ቅዱስ የተመሰከረው ትንሣኤዋና ዕርገቷ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ይልቁንም ሕፃናት ጭምር በደስታ የሚያከብሩት በዓል ቢኖር የድንግል ትንሣኤና ዕርገት መታሰቢያ ነሐሴ ፲፮ ቀን ነው ። ከዚያም በፊት የሐዋርያትን ጾም አርአያ በማድረግ ጾመ ፍልሰታን ከነሐሴ ፩ እስከ ፲፭ በታላቅ ፍቅርና ሱባዔ በጾምና በጸሎት ምዕመናንና ካህናት መናንያን ሁሉ ይፈጽሙታል ። በዚህ ርእስ እንደተጠቀሰው ከልጇ ትንሣኤ ጋር መዛመዱን በማስመልከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስክር ማቅረቡ ይመረጣል ። ስለሆነም በጥንታቂ ጥቅሶቹን በመዝሙረ ዳዊት " ተንሥእ እግዚእ ውስተ ዕረፍትከ አንተ ወታቦተ መቅደስከ " ይላል (መዝ. ፻፴፩ ÷ ፲) " አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ አንተና የመቅደስህ ታቦት " ማለት ነው ። ስለ ክርስቶስና ስለ እናቱ ስለ ድንግል ማርያም የተነገረ ትንቢት ነው ። ነቢይ አስቀድሞ ክርስቶስ እንደሚነሣ ከገለጠ በኋላ ቀጥሎ የመቅደሱ ታቦት (እናቱ) እንደምትነሣ ይናገራል ።

አቤቱ የሚለው ቃል ጌታ ሆይ ማለት ነው ነቢዩ ዳዊት ጌታ ሆይ የሚለው ማነው ? ከድንግል ማርያም በሥጋ የተወለደው የፍጥረቱ ሁሉ ጌታ በአባቱ ቀኝ ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። (መዝ. ፻፱ ÷ ፩ ፤ ማቴ. ፳፪ ÷ ፵፩ - ፵፮) ወደ ዕረፍትህ ተነሥ ማለት ምዕመናንን ወደ ምታሣርፍበት ወደ መንግሥተ ሰማያት ተነሣ ማለት ነው ዕረፍትህ የተባለችዋ መንግሥተ ሰማያት ናት ። በመንግሥተ ሰማያት ፍጹም ዕረፍት ይደረጋል ይኸውም በመንግሥተ ሰማያት የሰው ሁሉ ነፍስ የሚጨነቁበት መከራ ሥጋ መከራ ነፍስ የለም ። ሰዎች ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት ከመከራ ዐርፈው በደስታ ይኖሩባታል ። ይኸንን ሲገልጥ ሐዋርያው " እኛስ ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን " (ዕብ. ፬ ÷ ፫) ብሏል ።

# ሰቆቃወ ድንግል

ሦስትነት ባለው እግዚአብሔር
ስሙን አምኜ ልጀምር
የማርያምን ስደቷን
ዕንባ በማፍሰስ በሐዘን
እንደሰዋ ትኩዝ የሆነ ሰው
የመከራ ዕድል የደረሰው
ማሳዘኑ ፲ የተነጠለ ከወገኑ
ሰጊድ ሰላም
ወዴት አለፈች ከመንደር
ያምባሳው እናት ያቺ ጊደር
በግዜር አሳዩኝ መንገድዋን
እንድከተላት በሐዘን
እሳት አዝላ
ወዴት ባከነች ከገሊላ
ሰጊድ ሰላም
እግርሽ ጨረቃን የሚጫማ
ባሸዋ በጠጠር ስትሮጪ ደማ

ልጆሽን ልታድኚ በተሰዶ
ከሄሮድስ ፊት ከፉ ዘንዶ
መቸገርሽን ያን ሁሉ መከራሽን
ያየው
ድንጋይ ያለቅሳል እንኳን ሰው
ሰጊድ ሰላም
የገነት ፍሬ ጡቶችሽ
ነጥፈው ደረቁ ከገላሽ
የድንግልና ወተትን
የሚያፈልቁ ለመድኅን
በበረሃ የተንከራተትሽ እንደ ድሃ
ያ ! ሐሩር ስላንቺ ይፍጀኝ እንጂ ሣር
ሰጊድ ሰላም
መለኮት ልጅሽ እንደሌላ
ውሃ ተጠማ በዚያ ቆላ

ወደ ገጽ ፳፯ የዞረ

ዕረፍተ ነፍስ ወደ ሚገኝባት ሰማያዊት ኢየሩሳሌም (መንግሥተ ሰማያት) እንገባለን ማለቱ ነው ።

በመንግሥተ ሰማያት መከራ ሥጋ መከራ ነፍስ እንደሌለ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ " እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም የቀድሞው ሥርዓት አልፏልና " (ራዕ. ፳፩ ÷ ፬) ሲል የተገለጠለትን ጽፏል ። ክርስቶስ የምዕመናንን መከራ የራሱ መከራ አድርጎ እንደሚቆጥረው በመንግሥተ ሰማይ ዕረፍት ማግኘታቸውንም እንደራሱ ዕረፍት አድርጎ ይመለከተዋል ። ነቢዩም ወደ ዕረፍትህ ተነሥ ማለቱ የምዕመናንን ዕረፍት ለክርስቶስ ዕረፍቱ እንደሆነ ሲያሳስብ ነው ። ይኸንን አባባል በማነጻጸር ለመረዳት የሚከተለውን ንባብ እንመልከት " ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ ጌታ ሆይ ማነህ እንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ" (የሐዋ. ፱ ÷ ፬ - ፭) የክርስቲያኖች ስደት ጌታ ኢየሱስ የራሱ እንደሆነ የገለጠበት አንቀጽ ነው ።

ክርስቶስ ምዕመናንን በዚህም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም መንፈሳዊና ዘላለማዊ ዕረፍት ይሰጣል ። ስለዚህ ምዕመናንን በመንግሥተ ሰማያት ፍጹም ዕረፍት ስለሚሰጣቸው " ወደ ዕረፍትህ ተነሥ " ተብሎ ነቢይ ተናገረ ። በወንጌልም ክርስቶስ የዕረፍት የደስታ ምንጭና ባለቤት መሆኑ ተመስክሯል " እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ" እንደተባለ ።(ማቴ. ፲፩ ÷ ፳፰ - ፳፱ ) " ወደ ዕረፍትህ ተነሥ አንተና የመቅደስህ ታቦት " ይላል ። አንተ ተነሥ የመቅደስህም ታቦት ትነሣ ማለቱ ነው ተብሎ የተነገረለት ክርስቶስ መሆኑ ታውቋል ። የመቅደሱ ታቦት ማንናት ? የመቅደስህ ታቦት ትነሣ ሲልስ ምን ማለቱ ነው ?

ለጥያቄዎቹ ምላሽ ከመስጠታችን በፊት አንዳንድ ጥቅሶችን ብንመለከት ለትርጉሙ ቁልፍ ይሆኑናል ታቦትና መቅደስ በትድሚያ ምን እንደሆኑ በተለመደው አነጋገር ምሥጢራዊ ትርጉሙን ሳይሆን ገጸ ንባቡን እንደ እንመርምር ። ታቦት የጽላተ ሕግ ማደሪያ በውስጥና በአፍአ በወርቅ የተለበጠች በመቅደስ ውስጥ (በቅድስተ ቅዱሳን) ትኖር የነበረች የእግዚአብሔር ማደሪያ መገለጫ ዙፋኑ ናት በእግዚአብሔርና በሕዝበ እሥራኤል መካከል ውል ቃልኪዳን ናት ። እግዚአብሔር ለሰዎች ራሱን ገልጦ በታቦቱ ላይ ሆኖ የሚያነጋግርባት የክብሩ የጌትነቱ መገለጫ መታወቂያ ናት ። መቅደስ በአራቱ ቅድስተ ቅዱሳን የምትባለው የታቦቱ መኖሪያ እግዚአብሔር የሚመስገንበት ናት ። ቀድሞ በደብተራ ኦሪት ቅድስትና ቅድስተ ቅዱሳን በሚል ክፍል ተከፍሎ

www.ethiopianorthodox.org

ይታወቅ ነበር በኋላ በሰሎሞን ጊዜ ቤተመቅደስ ተሠራ ። ቤተ መቅደስ እግዚአብሔር የሚመሰገንባት የእግዚአብሔር ቤት ማደሪያ የታቦቱ መኖሪያ ናት ። (ዘጸ. ፳፭ ÷ ፰ ፣ ፳፩ - ፳፪ ፣ ዕብ. ፱ ÷ ፫-፬) ምድራዊት ቤተመቅደስ ታቦት የተሠራችው በሰማያት ቤተመቅደስና ታቦት አንጻር በዚያ ምሳሌ ነው በሰማይም ቤተመቅደስና ታቦት እንዳለ ተጽፏል ።

" እኔ እንደማሳይህ ሁሉ እንደማደሪያው ምሳሌ እንደ ዕቃውም ሁሉ ምሳሌ እንዲሁ ሥሩት በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ተከፈተ በመቅደሱ ውስጥ ያለችው የእግዚአብሔር የኪዳኑ (የሕጉ) ታቦትም ተገለጠች (ታየች)" (ዘጸ. ፳፭ ÷ ፱ ፣ ራዕ. ፲፩ ÷፲፱) በተለይ በራዕዩ ዮሐንስ የግዕዙ መጽሐፍ በሚገባ ይገልጣል ። " ወእምዝ ተርኅወ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ዘውስተ ሰማይ ወአስተርአየት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እንተ ውስተ መቅደሱ " ይላል ። ታቦቱ ተገለጠ ከማለት ታቦቲቱ ታየች ተገለጠች የሚለው ለምሥጢራዊ ፍቹ የቀና ይሆናል ስለዚህ ከአማርኛው ይልቅ የግዕዙ ቃል ይመረጣል ።

አሁን ወደ ጥያቄዎቹ መልስ እናምራ የመቅደሱ ታቦት ማን ናት የመቅደስህ ታቦት ትንሣ ሲል ምን ማለቱ ነው ? እንደሚታወቀው በመቅደስ ያለችዋ ታቦት የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆንዋ ባያከራክርም እንደ ሰው ነፍስ ኑሮዋት የምትኖር የምትነሣ ሆና የመቅደስህ ታቦትም ትንሣ ተብሎ ስለ እርሷ የተነገረ አይደለም ። በምድር ታቦተ ሙሴ በሰማይ ታቦት ዘዶር የተባለች የብርሃን ታቦት እንዳለች ቢታወቅም ሁለቱም ታቦታት መሞትና መነሣት ገንዘባቸው ወይም ጠባያቸው አይደለም ። ሞትና ትንሣኤ ግዕዛን ላላቸው ፍጥረታት የሚነገር ነው እንጂ ከዚህ ውጭ ለሆኑት አይነገርም አይታሰብም ታቦትም መቅደስም አይሞቱምና ካልሞቱ ተነሡ ማለት አይቻልም ።

" ታቦት " የሚለው ቃል ማደሪያ ማለት ነው የመቅደስህ ታቦት ሲል የመቅደስህ ማደሪያ እንደማለት ነው ይኸን አባባል በቁሙ እንዳለ ጥሬውን ወስደን እንተርጉም ብንለው አያስኬድም ። ምክንያቱም ታቦት በመቅደስ ውስጥ ይኖራል እንጂ ወይም መቅደስ ለታቦት ማደሪያው ነው እንጂ መቅደስ በታቦት ውስጥ አይኖርም አያድርም ይኸ ሊሆን የማይችል ነው ። በትንቢት የተነገረላት የመቅደስህ ታቦት የተባለችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት ። መቅደስ የተባለው በመቅደስ የተመሰለው በታቦቲቱ (በማደሪያው) ፱ ወር ከ፭ ቀን በማኅፀንዋ የኖረው በኋላም በክንዷ የታቀፈው በጀርባዋ የታዘለው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ቃልን ተዋሕዶ ከቃል ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆኖ የተገለጠው የክርስቶስ ሰውነት በቤተመቅደስ ተመስሏል እናቱ ማደሪያው ቅድስት ድንግል ማርያም በታቦት ተመስላለች ። የ ክርስቶስ ሰውነት በቤተመቅደስ ተመስሎ ቤተመቅደስ እንደሚባል ቅዱስ ወንጌል ያስረዳናል ። " ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተመቅደስ ይል ነበር " (ዮሐ. ፪ ÷፲፱ ና ፳፩) " ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት " ማለቱ በፈቃዱ ትገሉኛላችሁ በሞት ነፍሴ ከሥጋዬ እንድትለይ ታደርጋላችሁ ሲል ነው ። " በሦስት ቀንም እነሣዋለሁ " ማለቱ ደግሞ ከሞትሁ በኋላ በሦስተኛው ቀን ነፍሴን ከሥጋዬ አዋሕጄ ሰውነቴን እነሣዋለሁ ማለቱ ነው ።

" አፍርሱት " የሚለው ንባብ ከዚህ በላይ ባለው መንገድ የሚተረጎም ነው ። እንደ ዕሩቅ ብእሲ የክርስቶስ ሰውነቱ (ሥጋው) ይፈርሳል ይበሰብሳል (ሙስና መቃብር) ያገኘዋል ማለት አይደለም ስንኳን የክርስቶስ የእናቱ የድንግል ማርያም ሰውነት ሙስና መቃብር አላገኘውም ፣ እንዳያገኘው የአምላክ ታቦት ስለሆነ በክብር እስከ ትንሣኤም ተጠብቋል ። የክርስቶስ ሥጋው ሙስና መቃብር የማይደርስበት ስለመሆኑም የተነገረ ትንቢት አለ ። ፍጻሜውንም በግብረ ሐዋርያት ተጽፎ እናገኘዋለን ። " ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና ቅዱሳንህም መበስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም ። " (መዝ. ፲፭ ÷ ፲ ፣ የሐዋ. ፪ ÷ ፳፯)

" ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ አይቶ ነፍሱ በሲዖል እንዳልቀረች ሥጋውም መበስበስን እንዳላየ ተናገረ ። " (የሐዋ. ፪ ÷፴፩) " የመቅደስህም ታቦት ትንሣ " ማለቱ የአካልህ ማደሪያ እናትህ ድንግል ማርያምም አንተን በኩር አድርጋ እንደ አንተ እንደ ልጇ ትነሣ ማለት ነው ። የመቅደስህ ታቦት ድንግል ማርያም ስትሆን የመቅደስህ ታቦት ትንሣ ማለቱ ነው ። ከጻድቃንና ከኃጥአን ትንሣኤ አስቀድሞ እንደ ልጇ እንድምትነሣ በትንቢት የተናገረላት ድንግል ማርያም ብቻ ናት ። ጸጋን ከማግኘት ከሰው ልጆች ሁሉ ቀድሚያ እንዳላት በትንሣኤና በዕርገትም ከልጇ ከወዳጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር የሚቀድማት የለም አይኖርም ።

ጻድቃን በበጎች የተመሰሉት የክብር ትንሣኤ የሚነሡት በመጨረሻይቱ የፍርድ ቀን በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው ። ጻድቃን ክብር የሚያገኙበት ኃጥአን ፍዳ የሚቀበሉበት ዕለት ትንሣኤ ትንሣኤ ዘጉባኤ በሚል ስያሜ ትጠራለች በዚህ ስም ትታወቃለች ። ( ማቴ.፳፭÷፴፫ ፣ ዳን. ፲፪÷ ፪ ፣ ዮሐ. ፭÷ ፳፱ ) ተመልከት ።

እመቤታችን እንደሌሎች ጻድቃን ትንሣኤ ዘጉባኤ አትጠብቅም እንደ ልጇ ተነሥታ ዐርጋለች ። ዛሬ በልጇ ቀኝ ቆማ (ተቀምጣ) በመንግሥተ ሰማያት አለች ። ስለሊ ለነ ቅድስት ። (ቅድስት ሆይ ለምኝ ልን) ለሚሏት ሁሉ በተሰጣት የማማለድ የምሕረት ቃል ኪዳን ክርስቲያኖችን ስታማልድ ስታስታርቅ ትኖራለች ።

ታቦት ዘዶር የተባለችዋ ምሳሌዋ የምትሆን የብርሃን ታቦት በሰማያዊት ቤተመቅደስ እንድምትኖር እውነተኛይቱ ታቦት ድንግል ማርያም የአምላካችን የንጉሥ ክርስቶስ እናቱ በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ገብታ ስታማልደን ትገኛለች ። በልጇ በንጉሥ ክርስቶስ ቀኝ ሆና በክብር እንዳለች ስለ ንግሥቲቱ ስለ ድንግል አባቷ ዳዊት እንዲህ ሲል በትንቢት ቃል ዘምሮላታል ። ዛሬም ቤተክርስቲያን የድንግልን በዓል ስታከብር የዳዊትን መዝሙር በቅዳሴዋ ትዘምረዋለች ። ቃሉንም ከነትርጓሜው እናዋናው እንዘምረው። ትንሣኤዋን ዕርገቷን አምነን እንደ ልጇ ትንሣኤ አድርገን በደስታና በፍቅር እናከብር ።

" አዋልደ ንግሥት ለክብርከ ወትቀውም ንግሥት በየማንከ በአልባሰ ወርቅ ዑፅፍት ወኁብርት ። " (መዝ.፵፬ ÷ ፱ ) " የንግሥት ልጆች ለክብር (ለጌትነት) ናቸው ። ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቀመጣለች ወርቀ ዘቦ ግምጃ ደርባ ደራርባ ለብሳ

www.ethiopianorthodox.org

ተነናጽፋ ::" ትርጉሙም በአጭሩ " የእመቤታችን የመንፈስ ቅዱስ ልጆች ለጌትነትህ ይገዛሉ ። እመቤታችን በሰጠሀት ክብር ፀንታ ትኖራለች ፤ እንድም በቀኝህ ትቀመጣለች ። 'ወነበረተ ድንግል በየማን ወልዳ ወአምላክ' እንዲል ድንግል በልጇ በፈጣሪዋ ቀኝ ተቀመጠች ተብሎ እንደተነገረ ። ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና አንድ አድርጋ ይዛ በቀኝህ (በመንግሥተ ሰማይ በክብር) ተቀምጣለች።

የሰማይና የምድር ንግሥት የአምላክ እናት በንጽሕና በድንግልና ያጌጠች ሆና በክብር በልጇ አጠገብ በመንግሥተ ሰማያት በክብር እንዳለች መጽሐፍ ቅዱስ የመሰከረላትን ቃል ይዘን ትንሣኤዋን ዕርገቷን አምነን " ከመ ትንሣኤ ወልዳ " እንደ ልጇ ተነሣች ዐረገች በማለት ስንመሰክር እንኖራለን ።

ጣዕሟን ፍቅሯን ያሳድርብን ከትንሣኤዋ ከዕርገቷ በረከት ያሳትፈን። አሜን ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ።

# እ ማርያም

ያሬ ሰንብታ ሰንብታ
መጣች ለፍልሰታ
አገርሽ የት ነው ኤፍራታ
አሳድሪኝ ማታ
ይናፍቀኝ ሌሊት
የሰማይ እልፍኝ መብራት
ያሬ የኔ እመቤት
በክንፍሽ ጥላ ጋርደሽኝ
ከልጅሽ ሥፍራ ወስደሽኝ
እንዳልቆምብሽ በግራ
እንዳያስቃየኝ መከራ
ያሬ ነፍሴን አደራ
ንጽሕቴ ንጽሕቴ
እማልጅኝ በሞቴ
አንቺን ስለምን በልጅሽ ሳምን
ሲያል ይብላኝ ወይ እኔን



# ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር



www.ethiopianorthodox.org